በሱም ፡ እናድርግበት ፡ አሉ ። እኩሌቶቹ ፡ በደ
ንጊያ ፡ ወግረን ፡ እንግደለው ፡ አንጂ ፡ አይሆ
ንም ፡ አሉ ።
፳፭፡ አቤሜሌክና ፡ ባሮክም ፡ በዚች ፡ ሞት ፡ እትግ
ደሉት ፡ ብለው ፡ ጮሁላቸው ፡ አቤሜሌክና ፡ ባሮ
ክም ፡ ስለ ፡ ኤርምያስ ፡ አዘኑ ።
፳፮፡ ዳግመኛም ፡ ያያቸው ፡ የተሠወሩ ፡ ምሥጢሮ
ችን ፡ ይነግራቸው ፡ ዘንድ ፡ አልተዉትም ፡ ኤር
ምያስም ፡ ያየሁትን ፡ ሁሉ ፡ እስክስተምራችሁ ፡
ድረስ ፡ እኔን ፡ መግደል ፡ አይችሉምና ፡ አታል
ቅሱ ፡ አላቸው ።
፳፯፡ አሁንም ፡ አንዲት ፡ ደንጊያ ፡ አምጡልኝ ፡ አላ
ቸው ፡ እነሱም ፡ አንዲት ፡ ደንጊያ ፡ አመጡ
ለት ፡ እሱም ፡ አቆማት ፡ የዘለዓለም ፡ ብርሃን ፡
የምትሆን ፡ አንተ ፡ ይህነን ፡ ደንጊያ ፡ የሰው ፡
መልክ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ መልክ ፡
አድርግልኝ ፡ አለ ።
፳፰፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ደንጊያው ፡ ኤርምያስን ፡ በመ
ልክ ፡ የሚመስለው ፡ ሆነ ፡ ኤርምያስን ፡ መሰላ
ቸው ፡ ደንጊያውን ፡ በደንጊያ ፡ ይወግሩት ፡
ጀመር ፡ ወንጀሉንም ፡ ጨረሱ ።
፳፱፡ ኤርምያስ ፡ ግን ፡ ያያቸው ፡ ምሥጢሮችን ፡
ሁሉ ፡ ለአቤሜሌክና ፡ ለባሮክ ፡ ነገራቸው ፡ ይህ
ነንም ፡ ነግሯቸው ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ምግብና
ውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሄደ ፡ በሕዝቡ ፡
መካከል ፡ ቆመ ።
፴፡ ያንጊዜም ፡ ያ ፡ ደንጊያ ፡ እናንተ ፡ ሰነፎች ፡ የእስ
ራኤል ፡ ልጆች ፡ ኤርምያስን ፡ አስመሰላች
ሁኝ ፡ በደንጊያ ፡ ስለምን ፡ ትወግሩኛላችሁ ፡
ኤርምያስስ ፡ እነሆ ፡ በመካከላችሁ ፡ ቁሟል ፡
ብሎ ፡ ጮኸለት ።
፴፩፡ ኤርምያስንም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ደንጊያ ፡
ይዘው ፡ ወደሱ ፡ ሮጡ ፡ እሱም ፡ ምስክርነቱን ፡
ጨረሰ ፡ እሱንም ፡ ቀበሩት ፡ ያንንም ፡ ደንጊያ ፡
አምጥተው ፡ በመቃብሩ ፡ አፍ ፡ እንደ ፡ መዝ
ጊያ ፡ አድርገው ፡ አኖሩት ።
፴፪፡ የኤርምያስ ፡ ረዳቱ ፡ እነሆ ፡ ይህ ፡ ደንጊያ ፡
ነው ፡ ብለው ፡ በውስጡ ፡ ጻፉ ፡ የኤርምያስም ፡
የቀረች ፡ ነገሩ ፡ እነሆ ፡ በባሮክ ፡ መጽሐፍ ፡
ተጽፋለች ።
፴፫፡ እንቃቅቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ላስፈጸ
መን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በውነት ፡ ለዘለዓለሙ ፡
ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ባሮክ ፡ በዚህ ፡
መጽሐፍ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ተፈጸመ ።